የልጆች አስተዳደግ በዚህ ዘመን

ተግዳሮቶቹ እና መፍትሔዎቹ

ፊሰሐ ገ/ሃና

በካቸው ጫኪነ (ዶ/ር)

የልጆች አስተዳደግ በዚህ ዘመን

ተግዳሮቶች እና መፍትሔዎች

ፈሰሴ ገ/ሃና በላቸው ጨከነ (ዶ/ር)

ለንደን አዲስ አበባ

ግንቦት 2006 ዓ.ም./2014

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

©

All Rights are reserved.

የመጀመሪያ እትም መጽሐፍ

2006 ዓ.ም. (2014)

መጽሐፉን ለማግኘት:-

ኢሜይል: books@ethioamharic.com/

books4parent@gmail.com

ስልክ: +44 7908 949227 (**እንግሊዝ**)

+251 911 148852 (**ኢትዮጵያ**)

ድረ ገጽ: www.ethioamharic.com

ምስጋና

ከሁሉ አስቀድመን ይህን መጽሐፍ እንድናዘጋጅ ሃይል እና ጥበብ የሆነን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።

በመቀጠል ይህን መጽሐፍ ሙሉውን በማንበብ እና በማረም ለረዱን መ/ር ብርሃኑ አድማስ፣ ዲያቆን ታደለ ፈንታው እና ሀይሉ አብራሃም ታላቅ ምስጋናችንን እናቀርባለን። የመጽሐፉን የውጪ ሽፋን በመስራት እና አጠቃለይ የማማከር ስራ ላደርገልን ዲያቆን ሚሊዮን አጀበ ምስጋናችን የላቀ ነው። መጠይቅ በመመለስ እና የጋራ ውይይት በማድረግ ለተባባራችሁን ልጆች እና ወላጆች እንዲሁም ለስነ ልቦና ባለሞያዎች ምስጋናችን ይድረሳችሁ። የእናንተ ጎሳብ መጽሐፉን ሕይወት ሰጥቶታል።

ወ/ሮ ሜላት አስራት፣ መላአከ ሰላም ሞገስ አበበ፣ በጽዮን ሞገስ፣ ዮርዳኖስ በላቸው እና ኤፍራታ በላቸው የቤተሰብ ግዜያችሁን ስለሰጣችሁን እና ሁሌ ገንቢ አስተያየታችሁን ስላልተለየን ከልብ እናመሰግናለን። መጽሐፉን ለመጻፍ ቤተ ሙከራ ሆናችሁናል።

በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት በተለያየ መልኩ እገዛችሁ ያለተለየን አበራ ምስጋናው፣ ደረጀ ከበደ እና ስማችሁን ያልጠቀስን ሁሉ የከበረ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ፈሰሴ ገ/ሃና በላቸው ጨከነ (ዶ/ር)

መታሰቢያነቱ

አምላኩን የሚፈራ፣ በስነ-ምግባር የታነጸ፣ ማንነቱን የሚያውቅ፣ በሳይንስ የመጠቀ ልጅ ለማሳደግ ሁልግዜ ለምትደክሙ ለእናንተ ለወላጆች ይሁንልን።

ፈሰሴ ገ/ሃና በላቸው ጨከነ (ዶ/ር)

አርእስት ማውጫ ገጽ

መቅድም 5

መግቢያ 7

ምዕራፍ አንድ 10

ልጅ ምንድነው? 10

1.1 ልጅ ለወላጁ 11

1.2 ልጅ ለማኅበረሰብ 13

1.3 ልጅ ለሀገር 14

1.4 ልጆች በሥነ ልቦና ባለሙያዎች እይታ 17

ምዕራፍ ሁለት 20

2. የልጆች እድገት እና የጠባይ ለውጥ ከቅድመ ልደት እስከ ወጣትነት 20

2.1 ቅድመ ልደት 21

2.2 ድኅረ ልደት 23

2.2.1 ከ 0 እስከ 2 ዓመት ያሉ ሕፃናት መገለጫዎችና የሚፈልጉት ትኩረት 23

2.2.2 ከ 2 እስከ 6 ዓመት የሚገኙ ሕፃናት መገለጫዎችና የሚፈልጉት ትኩረት 27

2.2.3 ከ 6 እስከ 11 ዓመት የሚገኙ ልጆች መገለጫዎችና የሚፈልጉት ትኩረት 30

2.2.4 ከ 12 እስከ 17 ዓመት የሚገኙ ልጆች መገለጫዎችና የሚፈልጉት ትኩረት 32

ምዕራፍ ሶስት 37

3. ወላጆች ለልጆች ምን ሊያድርጉላቸው ይገባል? 37

3.1 መጫወቻዎችን እንደ እድሜያቸው ማቅረብ 37

3.2 ለልጆች የቴሌቪዥን ስርጭትና ፊልሞች መመጠን 41

3.3 ለልጆች አካባቢያቸውን ማስተዋወቅ 43

3.4 ከልጆች ጋር ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ 44

3.5 ልጆችን በትምህርት ማገዝ 45

3.6 ልጆችን የገንዘብ አያያዝ ማስተማር 46

3.7 ልጆች የሥራ ባህል እንዲማሩ ማድረግ 47

ምዕራፍ አራት 54

4. የተለመዱ የልጅ አስተዳደግ ዘይቤዎች 54

4.1 ወላጅ መር (አምባገነን) የልጅ አስተዳደግ ዘይቤ 54

4.2 አሳታፊ የአስተዳደግ ዘይቤ (Democrat parenting) 57

4.3 መረን የአስተዳደግ ዘይቤ 58

4.4 ቁብ የለሽ (ግድ የለሽ) የአስተዳደግ ዘይቤ 61

ምዕራፍ አምስት **64**

5. በልጆች የሚፈፀሙ ጥፋቶች እና የእርምት እርምጃዎች **64**

5.1 በልጆች የሚፈፀሙ ጥፋቶች መነሻቸው ምንድነው ? 64

5.2. ለጥፋት ማረሚያነት መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች 67

5.2.1 በባለሙያዎች የሚመከሩ የቅጣት ዓይነቶች 69

5.2.2 አዎንታዊ የሥነ ምግባር መገንቢያ ሥልቶች 72

ምዕራፍ ስድስት **74**

6. በልጆችን አስተዳደግ ወሳኝ ባለድርሻዎች እነማን ናቸው? **74**

6.1 ወላጆች 74

6.1.1 የወላጆች እና የልጆች የሕይወት ተሞክሮ 76

6.1.2 የዘመኑ ወላጅ በልጅ አስተዳደግ የሚገጥሙት ተግዳሮቶች 85

6.2 ማኅበረሰብ 88

6.3 ትምህርት ቤቶች 91

6.4 የሃይማኖት ተቋማት 92

6.5 መንግሥት 93

ምዕራፍ ሰባት 96

7. በውጪ ያሉ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በልጆች አስተዳደግ ያሉባቸው ችግሮች 96

7.1 የቅርብ ቤተሰብ አለመኖር 99

7.2 የቋንቋ እና የባህል ችግር 100

7.3 ስለ ልጆች አያያዝ የሚኖሩበት ሀገር ሕግ ወላጅ ካደገበት ባህል የተለየ መሆን 102

7.4 የቴሌቪዥን ተጽዕኖ 102

7.5 የኢንተርኔት እና የስልክ አጠቃቀም ችግር 103

7.6 ለልጅ የሚውል ጊዜ እጥረት 107

ምዕራፍ ስምንት 109

8. ምን አይነት ወላጅ ነዎት? 109

8.1 በእራስዎ የሚተማመኑ ወላጅ (with self-confidence)? 109

8.2 ለልጅዎ የሚያደርጉትን ለይተው የሚያውቁ ወላጅ? 112

ግጥሞች

ሻማ ነው 12

አንቺም ባለአዳነሽ 15

ምን ይለምኑ ይሆን? 61

ማነህ? 89

የለም የለም 107

መቅድም

የምንኖርበት ክፍለ ዘመን በብዙ መልካም እና መጥፎ ውስብስብ ነገሮች የተከበበ ዘመን ነው። ቀደም ባሉት ክፍለ ዘመናት እንደ ዋዛ የሚታለፉ በርካታ የሕይወት ሰልፎች ነበሩ። ዛሬ ግን እያንዳንዷ የሕይወት ርምጃ ብዙ ዋጋ ያስከፍላል። ከእነዚህ አሳሳቢ ጉዳዮች አንዱ ልጅን አሳድጎ ለቁም ነገር የማብቃት ጉዳይ ነው። አያቶቻችን አባቶቻችንን ያሳደጉበት ዘዴ ወላጆቻችን እኛን ያሳደጉበት የልጆች አያያዝ መንገድ ዛሬ ልጆቻችንን ለማሳደግ የሚያስችለን አይደለም። ዓለምና ነዋሪዋ፣ ማኅበራዊ ሥርዓታቸውን እና አኗኗራቸው በፍጥነት እየተለወጠ በትናንትና በዛሬ መካከል የትየለሌ ልዩነት እየተፈጠረ ነው። ስለዚህ ዘመኑ ስለልጆች አስተዳደግና አያያዝ ጠንቅቆ ማወቅን እና በጥበብ መጓዝን ይጠይቃል። ምን አደከመኝ ልጄቼ በዕድላቸው ይደጉ ብለን ችላ ለማለት አይቻለንም፤ ሰው አካሉን ችላ ይል ዘንድ ተፈጥሮው አይፈቅድለትምና። የሚቀጥለውን ትውልድ በትክክል አሳድገን ለቁም ነገር ለማብቃት የሚያስችለውን እውቀትና ክህሎት ለማግኘት ወላጅ ማንበብ፣ መወያየት፣ መጠየቅ እና መሰልጠን ያስፈልገዋል።

ብዙዎች ኢትዮጵያውያን ወላጆች ዘርፈ ብዙ በሆኑ ጊዜያዊ ችግሮች ተወጥረን ስላለን ትዳራችንን የምንመራውም ሆነ ልጆችን የምናሳድገው ዘልማዳዊ በሆነው ዘዴ ነው። አንዳንዱ ልጅን ሲያስበው ቁሣዊ ነገሮች ማሟላቱ ብቻ በቂ እንደሆነ ያስብና ትኩረቱ ማብላት፣ ማጠጣት እና ማልበስ ላይ ብቻ ይሆናል። አንድ አትክልተኛ ጥሩ ዛፍ የማሳደግ ራዕይ ይዞ ችግኝ ቢተክል በአግባቡ ውሃ ባያጠጣ የፀሐይ ብርሃን እንዲያገኝ ባያደርግ ያሰበውን

ቀጥ ያለ ዛፍ ላያገኝ ይችላል። የዛፉን ምግብ የሚሻማ ዕድገቱን የሚያቀጭጭ የዛፉን አቅጣጫ የሚያጣምም አረም ሊበቅል ይችላል፤ አትክልተኛው ጎበዝ ከሆነ በየጊዜው ሳይፈለግ የበቀለውን ተገቢ ያልሆነ አረም መንቀል አለበት። በዚያን ጊዜ ተክሉ በሚፈለገው መልኩ ቀጥ ብሎ ሊያድግ ይቸላል። በልጆች ሕይወትም የሚመለከተው ሁሉ የአሳዳጊነት ኃላፊነት የወሰደ ሁሉ የአትክልተኛውን ሚና መጫወት ይኖርበታል።

ልጆቻችን ከእኛ የተሻሉ እንዲሆኑ መመኘት እኛ ያጣነውን በእነርሱ በኩል ለማግኘት መቋመጥ ህልምን በልጆች ለመፍታት መሞከር በብዙ ወላጅ ልቡና የሚገኝ ነገር ነው። ዳሩ ግን ልጆቻችን ከመዳፋችን ከመውጣታቸውና ህልማችን ከንቱ ከመሆኑ በፊት እንደ ወላጅ መሠራት ያለባቸው ብዙ የቤት ሥራዎች አሉ። ከነዚህ መካካል አንዱ ስለልጆች አያያዝ እና የዕድገት ለውጥ ግንዛቤያችንን ማሳደግና ራሳችንን ለኃላፊነት ማዘጋጀት ኃላፊነታችንንም መወጣት ነው። ጤናማ አመለካከት ያለው እንቅስቃሴው፣ አለባበሱ፣ ቋንቋውና ፍልስፍናው ሁሉ የምንናፍቀው ልጅ እንዲሆን ለማድረግ የወላጆች (የአሳዳጊዎች) ሚና ወሳኝ በመሆኑ እያንዳንዱ ወላጅ ማወቅ፣ ለማወቅም መጠየቅ፣ ማንበብ፣ መማር፣ መጨነቅ ግድ ይለዋል። ይህ መጽሐፍም በዚህ በኩል ያለውን ጉድለት ለማሳየት እንደጠቋሚ ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

መግቢያ

ይህ መጽሐፉ በስምንት ምዕራፎች ተከፍሏል። የመጀመሪያው ምዕራፍ ልጅ ማለት ምን ማለት ነው? ብሎ ጠይቆ የልጅን ትርጉም ከቤተሰብ፣ ከማኅበረሰብ እና ሀገር አንጻር ዘርዝሮ ያስቀምጣል። ምዕራፍ ሁለት የልጆች ዕድገት፣ የጠባይ ለውጣቸውን እና ፍላጎታቸውን በስነ-ልቦና ባለሞያዎች እይታ አንፃር በየዕድሜያቸው አርከን ያስቀምጣል። ምዕራፍ ሦስት ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያቀርቡትን መጫወቻዎች፣ የቴክኖሎጂ እና የቴሌቪዥን አጠቃቀም፣ የልጆች የመስክ አይታ፣ የገንዘብ አያያዝ፣ የትምህርት አጠናን ዘዴን እና የልጆች የሥራ ባህል ምን መምሰል አንዳለበት ይዘረዝራል። በምዕራፍ አራት በአሁኑ ወቅት የተለመዱትን ወላጅ መር (አምባገነን)፣ አሳታፊ፣ መረን እና ቁብ የለሽ የተባሉትን የልጆች አስተዳደግ ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸውን ይተነትናል። በልጆች የሚፈጸሙ ጥፋቶችን እና የአርምት አርምጃዎችን ከባለሞያዎች አስተያየት አንጻር ምን መምሰል አንዳለበት በምዕራፍ አምስት ተጠቃሏል። ምዕራፍ ስድስት ውጤታማ እና ጤናማ ልጆችን ለማፍራት ባለድርሻ አካላት እነማን ናቸው ብሎ በመጠየቅ በልጆች አስተዳደግ የወላጆች፣ የትምህርት ቤቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት እና የመንግሥትን ሚና በዝርዝር ያስቀምጣል። በምዕራፍ ሰባት ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በልጅ አስተዳደግ ያሉባቸውን ችግሮች፣ መንሥኤዎች እና መፍትሔዎች ይዳስሳል። በመጨረሻው ምዕራፍ በልጅ አስተዳደግ ወላጅ የአለውን በራስ መተማመን እና ለልጅ የሚያስፈልጉትን መሰረታዊ ነገሮች እያደረገ እንደሆን ራሱን መመዘኛ ያስቀምጣል።

ይህ መጽሐፍ እነዚህን አርዕስተ ጉዳዮች በሰፊው ለመተንተን ይህንኑ የዘመኑ ከባድ የቤት ሥራ የሆነውን የልጆች አያያዝ በማሰመልከት በልዩ ልዩ ዘይዎች ከሀገር ቤት እና በባህር ማዶ ከሚገኙ ወላጆች፣ መምህራን፣ ልጆች እና ሌሎች አካላት መረጃዎችን በመሰብሰብ እና በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተጻፉ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን እና ጥናቶችን በመዳሰስ ቀጥተኛ የሕይወት ልምዶችን በመቀመር ጠቃሚ መረጃዎችን ለማካፈል የተዘጋጀ ነው።

ይህ መጽሐፍ በሦስት ነገሮች ከተለመደው የመጽሐፍ አቀራረብ ስልት ይለያል። በመጀመሪያ የልጆች አስተዳደግ በዚህ ዘመን በተጻፉ ጥናቶች ላይ በመመሥረት አንደኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም መረጃዎችን በመተንተን እና በተሞክሮ መልክ (Case study) በመግለጽ፤ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው ርዕሶች ኃሳቦችን በግጥም ስንኝ በማስቀመጥ እና አንባብያን መጽሐፉን ካነበቡ በኋላ ወላጅ አራሱን የሚመዝንበት አኃዛዊ መለኪያ ማስቀመጡ መጽሐፉን ልዩ ያደርጉታል። አንባቢ እንዳይሰለች ዋና ዋና ነጥቦችን በጉልህ ለማስቀመጥ ተሞክሯል።

በአጠቃላይ የቤተ ሙከራ ውጤት ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ብዙ ነጥቦች ተዳሰዋል፤ የባለሙያ አስተያየቶች ተካተዋል፤ ሁሉም ባለ ድርሻዎች ቢያነቡት በልጆች አያያዝ ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ የሚል እምነት አለን::

መልካም ንባብ::

ሻማ ነዉ

በወጉ ለኩሰዉ በክብር ካኖሩት፣

ከነፋስ ከወጀብ ከተከላከሉት፣

ብርሃኑ ያደምቃል ጨለማን ይገፋል፣

ፍቅርን እየዘራ ነፍስ ያለመልማል፣

የማያልቅ ተስፋም ይፈልቃል ከውስጡ፣

ከውሽንፍር ጋርደው በቅጥ ካስቀመጡ።

ፀዳል ለሕይወቱ፣

ትፍስሕት ለቤቱ፣

ልጅ ከነማዕረጉ ልጅ ከነ ዉበቱ፣

ሞገስ ነዉ ለቤቱ።

ልጅ ማለት ይሄ ነዉ፣

በፍቅር ከያዙት፣

በፍቅር ካከሙት፣

የሞት መድኃኒት ነዉ፣

የትዉልድ ሰንሰለት፣

ልጅ ሻማ ነው።

(ከፈሰሴ ገ/ሃና)